ቀን 02/6/2002 ዓ/ም

**የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን**

**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ ብሮድ ካስት ባለስልጣን ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር የፖለቲካ ፓርቲዎች በ2002 ዓ/ም ማለትም በዘንድሮው ምርጫ ለመወዳደርና ከወዲሁም ደጋፊዎቻቸውንና ህዝቡን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችላቸው የመገናኛ ብዙሃን የአየር ጊዜና የጋዜጣ አምድ ድልድል እንደሚያደርግ መግለፁ ይታወቃል።

በዚሁም መሰረት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ቅስቀሳ ለማድረግ የሚያስችላቸውን አምድ በምን መልኩ ቢያስተናግድ ተገቢ ይሆናል በሚለው ጉዳይ ከሚያሳትማቸው ጋዜጦች አንፃር መረጃ እንዲሰጥ ከባለስልጣኑ ተጠይቋል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ኮሚቴ አቋቁሞ የሚከተለውን ልኳል።

**የኮሚቴው አባላት**

1. ሠይፈ ደርቤ
2. አንተነህ ኃይለብርሃን
3. ሱልጣን መሃመድ ኑር

*1.* የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቦርዱና ብሮድ ካስት ባለስልጣን ባወጡት መስፈርት መሰረት የተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችን የቅስቀሳ ፅሁፍ የሚያስተናግደው በእለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣና በሳምንታዊው በሪሳ ጋዜጣ ነው።

**የገፆች ባህሪ**

- አዲስ ዘመን በአማርኛ ቋንቋ የሚታተምና አርበ ሰፊ ጋዜጣ ነው።

- በሪሳ ጋዜጣ በኦሮሚኛ ቋንቋ የሚታተምና አርበ ጠባብ ወይም ታብሎይድ የሚል ስያሜ ያለው ጋዜጣ ነው።
- አዲስ ዘመን ስድስት ኮለሞች አሉት፤
- በሪሳ አራት ኮለሞች አሉት፤
- ስለሆነም ከተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎቹ የምንቀበላቸው ፅሁፎች እነዚህን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

**የአቀባበሉ ሂደት**

- ፅሁፉ በጋዜጣው እንዲስተናገድለት የሚፈልገው አካል ወደ ድርጅታችን ከ24 ሰዓት በፊት የሚስተናገደውን ፅሁፍ ቢያቀርብ፣
- የተዓፈው ፅሁፍ፣ በሀርድ ኮፒና ሶፍት ኮፒ ቢደርሰን፣
- ምልልስ እንዳይበዛ ለማድረግ የሚላከው ፅሁፍ የግለሰቦችን፣ የህዝቡን መብት የማይነካ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ህገ መንግስቱን የማይፃረር መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ለበሪሳ የሚላከው ፅሁፍ ቢቻል በኦሮሚኛ ቋንቋ ተፅፎና በሶፍት ኮፒ ተደርጎ ቢላክ፣
- ፅሁፉን ወደ ድርጅታችን ይዞ የሚመጣው አካል በተቻለ መጠን አንድ የተወከለ ሰው ቢሆን፣ የላከውን አካል የሚወክል መታወቂያ ሊኖረው ይገባል፤
- የሚመጣው ፅሁፍ የላከውን አካል ማንነት የሚገልፅ ማህተም፣ ፊርማና ስም የሚገልፅ መሆን አለበት፣
- የሚላከው ፅሁፍ በግልፅ የሚታይና የሚነበብ መሆን አለበት፣

**ፓርቲዎች ሊገነዘቡት የሚገባ**

ፅሁፍን በማስተናገዱ ሂደት ከዚህ ቀጥሎ የሚዘረዘረው ኮለምና የፅሁፍ ብዛት የተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ዓርማን ጨምሮ የሚሰላ ነው። አንድ ኮለም ይህን ያህል

ገፅ ፅሁፍ ያስተናግዳል ሲባል ዓርማ ወይም ምስል አካትቶ ሊልክ የሚፈልግ ፓርቲ ምስሉንና ፅሁፉን በአንድ ላይ አካትቶ መጠቀም የሚገባው መሆኑን ታሳቢ ማድረግ አለበት። ፅሁፉን በተጠቀሰው ኮለም ልክ ልኮ ከዚያ በተጨማሪ ምስል ወይም አርማን እንደ ታሳቢ ቆጥሮ መላክ አይቻልም። ምክንያቱም ምስሉ በተጠቀሰው ፅሁፍ ላይ ሲደመር ፓርቲው ከተፈቀደለት ኮለም በላይ ይሆናል።

**የኮለሞች አወቃቀር**

**<u>አዲስ ዘመን ጋዜጣ</u>**

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ስድስት ኮለሞች አሉ። የአዲስ ዘመን አንድ ኮለም ማለት በሁለት ኤ4 ወረቀት ላይ በ12ፖይንት ሳይዝ የተፃፈ ፅሁፍ ብቻ ማለት ነው። ሁለት ኮለም ማለት በተመሳሳይ ነጥብና ወረቀት አራት ገፅ ፅሁፍ ማለት ነው። ሶስት ኮለም ማለት ስድስት ገፅ፣ አራት ኮለም ማለት ስምንት ገፅ፣ አምስት ኮለም ማለት አስር ገፅ፣ ስድስት ኮለም ማለት አስራ ሁለት ገፅ ይሆናል።

በዚህ ስሌት ግማሽ ኮለም ፅሁፍ ማለት በአንድ ኤ4 ወረቀት ላይ የተፃፈ አንድ ገፅ ፅሁፍ ማለት ይሆናል።

ፅሁፉ በፓርቲዎች በኤ4 ወረቀት ላይ ተፅፎ ሲቀርብ በፅሁፎቹ የላይኛውና የታችኛው ክፍተት መሃል የሁለት ፖይንት ክፍተት መኖር አለበት።

**በሪሳ ጋዜጣ**

የበሪሳ ጋዜጣ አራት ኮለም ፅሁፎችን የሚያስተናግድ ታብሎይድ ጋዜጣ ነው።

በበሪሳ ጋዜጣ ግማሽ ኮለም ማለት በግማሽ ገፅ ኤ4 ወረቀት ላይ በ12 ፖይንት ሳይዝ የተፃፈ ፅሁፍ ብቻ ማለት ነው። አንድ ኮለም ፅሁፍ ማለት በኤ4 ወረቀት ላይ በ12 ፖይንት ሳይዝ የተፃፈ አንድ ገፅ ፅሁፍ ማለት ነው። ሁለት ኮለም፣ በተመሳሳይ ሁለት ገፅ ይሆናል። ሶስት ኮለም ሶስት ገፅ ኤ4 ወረቀት፣ አራት ኮለም አራት ገፅ ኤ4 ወረቀት ላይ በተመሳሳይ ነጥብ የተፃፈ ፅሁፍ ነው። በፅሁፎቹ መሃል ከላይና ከታች ያለ የክፍተት መጠንም አንድ ከግማሽ ፖይንት ሳይዝ ነው።

**<u>ለሁለቱም ገፆች</u>**

ስሌቱ ዕሁፍን ብቻ ታሳቢ የሚያደርግ መሆኑን ማወቅ ይገባል:: አብሮ ምስል የሚላክ ከሆነ የተጠቀሰውን ነጥብና የፖይንት ሳይዝ መጠን ታሳቢ አድርጎ በወረቀቱ ላይ በተጠቀሰው መልኩ አሟልቶ መላክ ይገባል::

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት**

